# የራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች

## ገረመው 06-26-16

ከአፍሪካ አባል ሀገራት መካከል ደቡብ ሱዳንን በጥቂት አመታት በመብለጥ የአህጉራችንና የዓለማችን እንቦቀቅላ ሀገር ለመሆን የበቃችው ኤርትራ በውልደቷ ማግስት በገባቻቸው ሁለንተናዊ አረንቋዎች የተነሳ "የጨነገፉ ሀገራት" ተብለው ከሚጠቀሱ ጥቂት ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ መብቃቷ የአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሀን መዘባበቻ ከሆነ ሰነበተ።

ነፃነቷን አውጃ እንደ አንድ ሉዓላዊት ሀገር ሁሉ ዓለም ያወቀውን መንግስታዊ ማንነቷን አህዱ ብላ ለመጀመር የበቃችው ይህች የምስራቅ አፍሪካዊቷ ሀገር ገና በቅጡ እንኳን የጡጦ ዘመኗን ሳትጨርስና በመዳህ አቅም ላይ የነበረውን እንቅስቃሴዋን "ወደ ወፌ ቆመች" የዳዴ እርምጃ ሳታሳድግ ነበር ለጎረቤቶቿም ሆነ ለአህጉራዊና አለማቀፋዊ ሰላም ጠብ ጫሪ ለመሆን የበቃችው።

ለሰላሳ ዓመታት ለተካሄደው ጦርነት ልጆቿን በጦር እሳት በመማገድ ያለ የሌለ ሀይሏን አሟጣ በመጠቀም የነፃነት ነጋሪቷን ለመጎሰም ባለመቻሏ የተነሳ የደርግ መንግስትን አስወግዶ የበርካታ ህዝቦች ሀገር የሆነችውን ኢትዮጵያን ለማስተዳደር የሽግግር መንግስት ያቋቋመው የኢህአዴግ መንግስት በፈቀደው "የሪፈረንደም" እድል የተነሳ ነፃ ሀገር ለመሆን የበቃችው የመከረኛ ህዝቦች አገር አርትራ ነፃነቷን በተጎናፀፈች ማግስት የገጠማት ክፉ አበሳ የታዳጊ ህፃን ሀገር የነፃነት ሽግግር ከወታደራዊው ደርግ ወደ የበረሀዊው ደርግ ያሸጋገረ ለመሆን መብቃቱ የህዝቦቿን ህልውና ምላጭ የሚያስውጥ እንዲሆን አብቅቶታል።

በነፃነት ማግስት ኤርትራ አፍሪካዊቷ ሲንጋፖር  የያዘውን ህልም የሚያሳካበት አቋም እንደሌለው ያረጋገጠው አገሪቷን የመምራት ዕድል እጣ የተረከበው የሻዕቢያ መንግስት የራሱን እድሜ እና ህልውና ለማሰንበት ሲባል ብቻ አገሪቷን "በሉዓላዊነት" ስም ወደ ተለያዩ ጦርነቶች የማስገባትና በዚህ አብይ አጀንዳ ህዝቦቿን ሰቅዞ በመያዝ የአገዛዝ ዘመኑን ለማጠንከር በማሰብ ወደ ለየለት ወታደራዊ አምባገነንነት በመለወጥ ህዝቦቿንና ልጆቿን ፋታ ባላገኙበት ጦርነት ወደ ክፉ ጦርነት እንዲሸጋገሩ ለማስገደድ ችሏል።

የልደታ ቀንን ለማክበር ሻማ ለማብራት የሚሆን ክብሪት ለመለኮስ የሚያስችላት ጠንካራ እጅ እንኳን ሳይኖራት "እርም" ብላ ልትተወው ወደሚገባት ጦርነት ለመመለስ እጅግ በጣም የፈጠነችው ኤርትራ እንዳሻው ያደርጉት ዘንድ "ሜዳውም ፈረሱም ይሄው " ተብሎ የተፈቀደለት የሚመስለው የኤርትራ መንግስት በሀኒሽ ደሴቶች የይገባኛል

ጥያቄ ቀይ ባህርን ተሻግራ የምትገኘዋን የመንን ለመውረር በጦር ሀራራ ስልጣኑን የማቆየት ስትራቴጂውን የማሳካት ህልሙን ለመጀመር ያዘገየውም አልነበረም።

እየለየለት በመምጣት የአለማችን እጅግ የከፋ ስርዓት ወደ መሆን ደረጃ የተሸጋገረው የፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፍወርቂ መንግስት እንደ ሱዳን ኢትዮጵያንና ጅቡቲን የመሳሰሉ ሀገሮች የጀመሩትን ሰላማዊ ልማታዊ ጉዞ ለማደናቀፍና የራሱን የስልጣን ዘመን ለማራዘም የያዘውን ስትራቴጂ እውን ለማድረግ በያዘው ብርቱ አቋም የተነሳ የጦርነት ነጋሪት በመጎሰም ሰራዊት አዝምቶ ደም አፋሳሽ ጦርነት ውስጥ እንዲገቡ ያስገደዳቸው ግጭት መጠንሰሱና መጀመሩ ሳይሆን ቡና አጣጪው ጎረቤቶች ወደ አልሆኑት ሱማሌና ሌሎች ሀገራት ዘው ብሎ በመግባት ትርምስ ወዳድነቱን እያረጋገጠ ለመጓዝ በቅቷል።

የውጭ ፖሊሲው ባህርይው ይህንን በመሰለ ጠብ አለሽ በዳቦ የጦርነት ስትራቴጂ ላይ የተመሰረተው ኢሳያስ መራሹ የሻዕቢያ አስተዳደር ጦርነት የመረረውንና ያንገሸገሸውን ሰፊውን የኤርትራ ህዝብ ከጦር ወደ ጦር ለማሸጋገር የቻለበትን የእሳት ድልድይ ከመገንባት በዘለለ የሀገር ውስጥ አምባገነናዊ መዳፉን በማጠንከር ወደ ለየለት አረመኔያዊና ነፍሰበላነታዊ ባህርይ የለወጠበትን ቅርጽ ለመያዝ መቻሉ የዚያችን መከረኛ ሀገር ህዝቦች ህልውና አጠያያቂ ለማድረግ ብዙም ጊዜ አልፈጀበትም።

አብረው ከኖሩት ጋራ አብሮ አርጅቶ የኢሳያስ መንግስት ለኤርትራና ለህዝቦቿ ነፃነት ሲሉ በትጥቅ ትግሉ ብርቱ ትግል ያደረጉ ታላላቅ ታጋዮችና መሪዎችን"የእነሱ ጥያቄ አግባብነት የለውም" በሚል አቋም ደብዛቸው እንዲጠፋ ማድረጉ በህዝቦችም ሆነ በተቀረው የአለም ህዝቦች ድንጋጤ መፍጠሩ ሲታወስ የሻዕቢያ አመራር ወደ የትኛው የለየለት አቅጣጫ መጓዝ መጀመሩን ፍንጭ በመስጠት ረገድ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ሆኖ ሊነሳ የሚችል የለየለት አምባገነናዊ ጅማሮ መሆኑ አይጠረጠርም።

አሁን ድረስ የታሰሩበትን አካባቢም ሆነ ስለ ህልውናቸው ቤተሰቦቻቸው እንኳን ምንም ዓይነት ፍንጭ ለማግኘት ያልቻሉት የቀድሞ የኤርትራ ባለስልጣናትና ጋዜጠኞች ያሉበት ትክክለኛ እውነታ አለመታወቁም ሆነ ፍርድ ቤት ደጃፍ በመቅረብ ፍትህን የማግኘት ሰብዓዊ መብትን እንኳን ለማግኘት አለመቻላቸው የአደባባይ ሚስጢር በሆነበት በዚያች ከእድሜዋ በላይ የግፍ ቀንበር ለመሸከም በተገደደች ታዳጊ ሀገር አለም በይፋ አውቆና ቆጥሮ "የት ገቡ" ብሎ በሚጠይቃቸው ከእነዚህ የአምባገነናዊ መንግስት ሰለባዎች ባሻገር በቀን ተቀን ደብዛቸው የሚጠፋና በየወታደራዊ ካምፕ ታጉረው አበሳቸውን የሚቆጥሩ ዜጎች ቁጥር ቀላል ተብሎ የሚታለፍ አይደለም።

ኢሳያስ መራሱ የአስመራ መንግስት የያዘው ጽንፍ የሳተ አምባገነናዊ ተግባሩ መፈናፈኛ ያሳጣቸው ዜጎቿ ወደ ከፋው ደርጋዊ አስተዳደርነት የተለወጠውን አመራር በመሸሽ ወደ ሌሎች ሀገራት በማምራት የሚያደርጉትን የነፍስ አድን

እሩጫ ድንበር ላይ ለመግታት የሚሞክሩ ታማኝ የመንግስት ወታደሮች የሚተኩሱት ጥይት ለመዳን ያላቸው እድል ጠባብ መሆኑን ቢያውቁትም መጋፈጥ የማይችሉትን አረመነኔያዊ መንግስት ለመሸሽ የድንበር ላይ አልሞ ተኳሽ ጥይቶችን መጋፈጥ ብቸኛው አማራጭ አድርገው መውሰዳቸው "ሲንጋፖራዊቷን ኤርትራንና ህዝቧን ነፃ አውጥቻለሁ" በሚለው አመራር ላይ እየተጠናከረ የመጣው ጥላቻ የቱን ያህል የመረረና የጠነከረ እንደሆነ በተጨባጭ በማሳየት ላይ ይገኛል።

የአምባገነኑ መንግስት ታማኝ ወታደሮች የሚያርከፈክፉት የጥይት ዝናብ ለማምለጥ የታደሉ የኤርትራ ወጣቶች የዓለማችን አደገኛ የስደት መስመሮች የሆኑትን የቀይና የሜዴትራንያን ባህሮችን ገላ ማጠቢያ ሳፋ በሚያካክሉ ጀልባዎች ታጭቶ አሳዛኝ እጣ ፋንታ ላይ ለመውደቅ መገደዳቸው የሚያስከፍላቸው ልክ ያለፈ መስዋእትነት እንዳለ የሚረጋገጥላቸው ቢሆንም ከኢሳያስ አስተዳደር ይልቅ ይህንን አደገኛ ጉዞ እንደመፍትሄ አማራጭ አድርገው መውሰዳቸው አሁንም በዚያች ሀገር ሁሉም ነገር ሳይነጋ ማምሸቱን ለማረጋገጥ የቻለ ሀቅ ሆኗል።

የተስፋ ጎህ ያዩላትን ሀገራቸውን ሳይነጋ የማምሸት ትዕይንት በማመን በተለያዩ አቅጣጫዎች ሀገራቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ለመውጣት የተገደዱ ወጣቶች "ለነፃነታችሁ ታገልኩላችሁ" ከሚለው የመንግስት ወታደር ጥይቶች በማምለጥ የባህር አሳ ነባሪ ሲሳይ ለመሆን ተገደዋል።ከዚህ ዓይነት አሳዛኝ እጣ ፋንታ የተረፋም ቢሆኑ ዛሬ በእርስ በርስ ጦርነት በሌሎች ምክንያቶች የጦር አውድማ ከሆኑት ከእነ አፍጋኒስታን፣ ኢራቅና ሶርያ በመቀጠል አርትራ የአለማችን መራር የስደት እጣ ፋንታን በመጋፈጥ ላይ ያሉ ህዝቦችን በማስመዝገብ ስሟ ቀን ተሌት እንድትነሳ አድርጓል።

የኢሳያስ መንግስት መራሩን ገፈት እንዲቀምሱ ያስገደዳቸውና የዕለት ተዕለት ጉዟቸውን በምላጭ ማሳ ላይ እንዲመሰረት ግድ የተባለላቸው የኤርትራ ህዝቦች ከዚያ አምባገነናዊ አስተዳደር ለማምለጥ ጎረቤት ሀገር ኢትዮ'ያን እንደ ሁነኛ ወዳጅ በመቁጠር የተሻለ አማራጭ ለማድረግ መቻላቸው "ከለላችን" ብለው የሚመጡ ዜጎች ሁሉ የተሻለች እናት መሆኗን ለምታረጋግጠው ኢትዮጵያ "ደከመኝ ሰለቸኝ" የማያሰኝ ባይሆንም አገራችንን ቁጥር አንድ ጠላቱ አድርጎ በውጭ ፖሊሲው ላይ ለፈረጃት የኤርትራ መንግስት እንቅልፍ የሚነሳ የእንሶላ ውስጥ እሳት ሆኖበታል።

በህዝብ ለህዝብ መግባባት ላይ የተመሰረተውን ፖሊሲዋን በመያዝ ጠላቷ በሆኑ መንግስታትን ከሰላም ወዳድ ህዝቦች ነጥሎ በማየትና በማስቀመጥ ስልት እየተጓዘች የምትገኘው ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገር ኤርትራ ህዝቦች እንደ አንድ የስደት አማራጭ በመሆኗና ከአምባገነኑ አስተዳደር ለሸሹት ንፁህን ስደተኞች በምቹነት ተመራጭ ለመሆን በመብቃቷ

በቀን ከመቶዎች በላይ የሚቆጠሩ ኤርትራውያን ዜጎች "መጠጊያዩ" ብለው የስደቱን ግንባር አቋርጠው ለመግባት የቻሉበትን ሀቅ በተጨባጭ እያሳየ ይገኛል።

እየዋለ እያደረ የሚያራምደው አምባገነናዊ ስርዓት በአለም መንግስታት ፊት እየታወቀ የመጣው የኤርትራ መንግስት በህዝቦች ላይ የፈፀመው እጅግ ሰብዓዊነት የጎደለው አረመኔያዊ ተግባር በጥናት ሊረጋገጥ በመቻሉ የመከራ ገፈት እየቀመሰ የሚገኘውን ህዝብ ለመታደግ ቁርጠኛ አቋም ለመያዝ የቻለው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የአምባገነኑ መንግስት ባለስልጣናትን በጦር ወንጀለኝነት ለመክሰስ የመጨረሻ አቋም ለመያዝ መብቃቱ በምድራቸው ዴሞክራሲያዊ መንግስት ለመመስረት የመጀመሪያው አማራጭ ራሳቸው ብቻ ለሆኑት ኤርትራውያን እንደ መልካም ብስራት የሚቆጠር ሆኗል።

የሀገሪቱ መከራ እጅግ መራር ሆኖ በየእለቱ የስደት አማራጮችን ሁሉ በመጠቀም ጥለው የሚሸሸው ዜጋዋ ቁጥር እየጨመረ በመምጣት ቀስ በቀስ ሰው አልባ ምድር ወደመሆን ደረጃ በመሸጋገር ላይ ለምትገኘው ኤርትራ ቢዘገይም እንኳን ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የተደመጠው አቋም እሰየው የሚያሰኝ በመሆኑ በያሉበት ሀገር ድጋፋቸውን የሰጡበትን ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ የቻሉበትንና የውስጣቸውን እምቅ መልዕክት ለማስተላለፍ የበቁበትን መልካም እድል አግኝተዋል።

በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት በሚገኙ ከተሞች ነዋሪ የሆኑ ኤርትራውያን የተመድ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በአምባገነኑ የኤርትራ መንግስት ላይ የያዘውን ጠንካራ አቋም እና የወሰደውን የክስ ውሳኔ በመደገፍ እጅግ የተጠናከረ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ላይ በሚገኙበት በዚህ ወቅት "እናት ሀገሬ" የሚሏትን ታዳጊ ሀገር እየመራ የሚገኘው የአምባገነናዊ መንግስት ያልሰጣቸውን ሙሉ መብት በማግኘት በአዲስ አበባ፣ በትግራይ እና ዓፋር አካባቢዎች ለኮሚሽኑ ውሳኔ ሙሉ ድጋፍ ለመስጠት እጅግ የተጠናከረ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ በኢሳያስ መራሹ አመራር ላይ ያላቸውን ምሬት በከፍተኛ ደረጃ አንፀባርቀዋል።

ወላጆቻቸውን በአምባገነናዊ መንግስት ግፍ የተነጠቁ ህፃናት ከፊት ቀድመው በወጡበትና ወጣት ወንዶች ፀጉራቸውን ተላጭተው ሴቶች ደግሞ ጥቁር ልብስ ለብሰው የከረረ ምሬታቸውን ባሳዩበት ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የአምባገነኑ መሪ ምስል ያቃጠሉ ኤርትራውያን ስደተኞች ሌሎች ወገኖቻቸው በበረሀና በባህር ወድቀው መቅረታቸውን በማስታወስና በኢትዮጵያ ይህንን የመሰለ እድል ማግኘታቸውን በማመስገን የተባበሩት መንግስታት ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የያዘው አቋም ተጠናክሮ በመቀጠል በፍጥነት ወደ ውጤት የሚያመራበት አሰራር ተግባራዊ እንዲሆን ተማጽነዋል።

የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የኤርትራ መሪዎችን በጦር ወንጀለኝነት ለመክሰስ የያዘው አቋም በፍጥነት ወደ ፍርድ ቤት ቀርቦ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚሹ ኤርትራውያን ከኮሚሽኑ አቋም ጋር መቆማቸውን በአንድ

ድምጽ እያስተጋቡ መሆናቸው ያችን ካለእድሜዋ በተሸከመቻቸው አምባገነኖችና ጦርነቶች የገበጠችውን ሚጢጢ ሀገር ቢያንስ ሰው አልባ ምድር ከመሆን እንደሚታደጋት ማመናቸውን በተጨባጭ ያሳያል።

ይህንን የመሰለ አስከፊ ሁኔታ ላይ የሚገኘው የሻዕቢያ መንግስት የኢትዮጵያን እና የጎረቤት ሀገሮችን ሰላም ለማደፍረስ የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ በመቀጠል ያልተሳኩ ተግባሮችን ለመፈፀም ሲጥር ማየት የተለመደ ክስተት ሆኗል።ይባስ ብሎ ከሰሙኑ የዚህ አምባገነን መንግስት የአማርኛ መርሀ ግብር በሆነው የአርበኞች ግንቦት 7 ልሳን በሆነው እርግጥነቱ በማያጠያይቀው ኢሳት ቴሌቭዥን ጣቢያ እና በሀገሪቱ ቴሌቭዥን ፕሮግራም "ጠብቁኝ" እያለ በማስተላለፍ ላይ የሚገኘው እንቶ ፈንቶ ማስታወቂያ የዚህ አካል የቀቢፀ ተስፋ እንቅስቃሴ ከማሳየት የዘለለ ፋይዳ የለውም።

"በኢትዮጵያ የብሄራዊ መረጃና ደህንነት ተቋም የሚሰሩ 40 ሺህ ሰራተኞና ባለስልጣናት ማንነትና አድራሻ በይፋ አሳውቃለሁ ይህ ተቋም በኢትዮጵያ ላይ እየፈፀመ ያለው ግፍ ግፍና በደል አጋልጣለሁ" በማለት ላይ የሚገኘው የኤርትራ የደህንነት ቢሮ "የእራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች" እንዲሉ ከዚህ ቀደም ተደጋግሞ እንደተገለፀው እንደ ፍየል የራሱን ገበና መክተት ያልቻለበትና ጥብቅ አሰራር የሚጠይቀውን የደህንነት ስራ በአግባቡ አለመወጣቱ እየታየ የጎረቤት ሀገሮችን ምስጢር ለመበርበር የሚችልበት አቅም እንደሌለው በተጨባጭ የሚያሳይ መሆኑ አይካድም።

መነሻቸውን አስመራ ላይ ያደረጉ የተለያዩ የሽብር ጥቃቶች በተለይ አቅጣጫቸው ወደ ኢትዮጵያ ሲንደረደሩ ገና ከመነሻቸው በሚያገኘው ጥብቅ የደህንነት ሚስጢር ተከታትሎ የገቡበት ገብቶ የመያዝ ብቃቱን ደጋግሞ ያስመሰከረው የኢትዮጵያ ብሄራዊ የመረጃና የደህንነት ተቋም ሀገሪቱንና ህዝቦቿን ከማንኛውም ዓይነት የሽብር ተግባራት ለመከላከል የቻለው እንደ ሻዕቢያና አርበኞች ግንቦት 7 የመሳሰሉ ሀይሎች ልቆ በመገኘ ስራቸውን ተከታትሎ የማንበርከክ ብቃት ስላለው ብቻ ሳይሆን የራሱን ሚስጢር ለመጠበቅ የሚችልበትን አስተማማኝ ጥንካሬ በማካበቱ በመሆኑ በፍፁም ሊዘነጋ አይገባም።